መልእክት ስድስት

## ለጌታ ክፍት ዕቃ መሆን እና ዘወትር ቀኖቻችንን በመለኮታዊው ሥላሴ መለኮታዊ እደላ ውስጥ መኖር

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ዘፍ. 2፡7፤ ሮሜ 9፡21-23፤ 2 Cor. 4፡7፤ 2 ጢሞ. 2፡20-21

**I. ዓላማውን በመፈጸም ውስጥ የእግዚአብሔር አካሄድ የመጀመሪያው እርምጃ እርሱን የሚይዝ ዕቃ አድርጎ ሰውን መፍጠር ነበር—ዘፍ. 2፡7፡-**

ሀ. እግዚአብሔር በሦስታንዱ አምላክ የተሞሉ የክብር ዕቃዎች እንድንሆን መረጠን—ሮሜ 9፡21-23፤ 2 ቆሮ. 13፡14፡-

1. እግዚአብሔር እርሱን የሚይዝ ዕቃ አድርጎ ሰውን ፈጠረው፣ እርሱን፣ የክብርን አምላክ፣ እንድንይዘው የክብር ዕቃዎች እንድንሆን ከብዙ መያዣ ዕቃዎች እኛን መረጠን—4፡7።
2. የክብር ዕቃዎች ከመለኮታዊው ባሕርይ (ከወርቅ) እና ከተዋጀው፣ ዳግም ከተወለደው የሰብዕና ባሕርይ (ከብር) ከሁለቱም የተቀናበሩ ናቸው—2 ጢሞ. 2፡20-21።
3. የክብር ዕቃዎች እንድንሆን እግዚአብሔር ክብሩን በእኛ፣ በመያዣ ዕቃዎቹ ያሳውቃል—ሮሜ 9፡23፤ 2 ቆሮ. 3፡18፤ 4፡6-7፡-

   ሀ. ይህ ሁሉ ከምሕረቱ የተነሣ እና በምሕረቱ መሠረት ነው፤ በጥረቶቻችን ሊገኝ አይችልም።

   ለ. በዚህ ምክንያት ስለ ምሕረቱ እርሱን ማምለክ እና እርሱን ማመስገን አለብን—ሮሜ 9፡15-16፣ 18።

ለ. የሐዋርያው ጳውሎስ አሥራ አራቱ መልእክቶች ማጠቃለያ በሁለት ቃላት ሊገለጽ ይችላል፡- *ክፍት ዕቃ*፡-

1. አዲስ ኪዳን እግዚአብሔር እርሱን እንደሚወዱ እና ለእርሱ ራሳቸውን ክፍት አድርገው እንደሚጠብቁ መያዣ ዕቃዎች አማኞችን እንደሚፈልግ ያሳያል—2 ቆሮ. 3፡16፡-

   ሀ. በማንነታችን ጥልቀት ለጌታ ክፍት ካልሆንን፣ ራሱን ወደ ውስጣችን ማደል እና ቤቱን በልባችን ውስጥ መሥራት አይችልም—ኤፌ. 3፡17።

   ለ. ክፍት የሆነ መያዣ ዕቃ በመለኮታዊው ሥላሴ መለኮታዊ እደላ ለመሞላት ራሱን ክፍት ከማድረግ ውጭ ምንም ነገር አያደርግም—2 ቆሮ. 13፡14።

2. እውነተኛ የክርስቲያን ሕይወት ጌታን የሚወድ እና የራሱን ድርጊት አቁሞ ለጌታ ራሱን ክፍት አድርጎ የሚጠብቅ ነው—ማር. 12፡30፤ 1 ዮሐ. 4፡16-21፡-

   ሀ. ያኔ ጌታ ይመጣና ሁሉንም ነገር ያደርጋል፤ ያ ዕቃ ጌታን ይይዛል፣ የጌታን መሙላት እና ድርጊትም ይደሰታል።

   ለ. ጌታ ማድረግ የሚፈልገውን ሁሉ እንዲያደርግ ለእርሱ እያንዳንዱን ዕድል በመስጠት ጌታን መውደድ እና ለእርሱ ራሳችንን ክፍት አድርገን መጠበቅ ያስፈልገናል—ኤፌ. 3፡17።

   ሐ. ይህ ተገቢው እና እውነተኛው የክርስቲያን ሕይወት ነው—ገላ. 2፡20።

3. "ጌታ ሆይ፣ በጸጋህ የትኛውንም የማንነቴን ክፍል ለአንተ ዝግ አላደርግም፤ ራሴን ሙሉ በሙሉ እና በዝርዝር ለአንተ ክፍት አድርጌ መጠበቅን እመርጣለሁ" ብለን መጸለይ አለብን፡-

   ሀ. ይህ ተገቢ ጸሎት፣ ጠለቅ ያለ ጸሎት፣ እውነተኛ ጸሎት ጌታን መውደድ እና ለእርሱ ክፍት መሆን ነው—ኤፌ. 1፡17-19።

   ለ. እንደዚህ ዓይነት ጸሎት ካለን፣ ሕያው፣ ክፍት መያዣ ዕቃዎች እንሆናለን፣ ጌታም በራሱ ይሞላን ዘንድ መንገድ ያገኛል—3፡14-18።

   ሐ. ጌታ ሲሞላን፣ ሁሉንም ነገር ያደርግልናል—ቁ. 19።

**II. በክርስቶስ እንደሚያምኑ ሰዎች ዘወትር በሚኖረን ሕይወት በመለኮታዊው ሥላሴ መለኮታዊ እደላ ውስጥ ባሉ የዘወትር እና የወትሮ ልምምዶች መርካትን መማር ያስፈልገናል—ሮሜ 8፡2፣ 6፣ 10-11፤ ኤፌ. 3፡16-17፡-**

ሀ. ይህን እደላ ቀስ ባለ፣ መደበኛ በሆነ መንገድ ደጋግመን በመቀበል መለኮታዊውን እደላ ጥቂት በጥቂት ዕለት ዕለት መቀበል ያስፈልገናል—2 ቆሮ. 13፡14፤ ማቴ. 6፡11፤ መዝ. 68፡19፡-

1. ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በውስጣችን የሚፈጸሙት መንፈሳዊ ነገሮች ጥቂት ናቸው፤ ይልቁንም ልክ እንደ የአካላችን ሕይወት፣ አብዛኞቹ መንፈሳዊ ነገሮች እንደገና መደጋገም አለባቸው—ዮሐ. 6፡57፤ 4፡14፤ 1 ቆሮ. 10፡3-4።
2. እግዚአብሔር የሚሰጠን ማንኛውም ነገር መሸከም ከምንችለው በላይ እንዳይሆን በአንድ ጊዜ አይደለም፤ በምትኩ መለኮታዊው አቅርቦት የሚሰጠን ጥቂት በጥቂት ነው።

ለ. በሂደት ያለፈው እና የተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ በውስጣችን ያለው በአስደናቂ መንገድ ሳይሆን በተለመደ መንገድ ነው፤ ስለዚህ ምክንያት መደበኛ እና የወትሮ የክርስቲያን ሕይወት መኖር ያስፈልገናል፤ ልዩ መሆናችን ሲቀንስ እና ይበልጥ ወትሮአዊ ስንሆን፣ የተሻለ ነው—ቆላ. 1፡27፤ 3፡4፤ ኤፌ. 3፡16-17።

ሐ. ሦስታንዱ አምላክ በመለኮታዊው እደላ የሚሰጠን የሕይወት ነገሮች ሁሉ ጸጥ ያሉና የተረጋጉ ናቸው፣ እንደ አማኞች ያለንም ሕይወት እንዲሁ ጸጥ ያለ እና የተረጋጋ መሆን አለበት፤ መኮታዊውን እደላ የመቀበል የተለመደ ሕይወት በመኖር ዕለት ዕለት በዚህ መንገድ መኖር ያስፈልገናል—ሮሜ 8፡6፤ 1 ተሰ. 5፡23፤ 2 ተሰ. 3፡16።

መ. እጣ ፈንታችን በመለኮታዊው ሥላሴ መለኮታዊ እደላ የተለመደ ሕይወት መኖር ነው፣ ምክንያቱም አባታችን በእርሱ የማያቋርጥ እደላ ሥር በተለመደ መንገድ እንድንኖር ወስኖአልና—ማቴ. 6፡11፣ 32-34፤ 24፡40-41።

ሠ. እንደ አማኞች የመለኮታዊውን ሥላሴ መለኮታዊ እደላ በእምነት እንለማመዳለን፤ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር እንድናደርግ የሚፈልገው በእርሱ ላይ በመደገፍ፣ እርሱን እንደ ሕይወት በመውሰድ እና ራሱን ወደ ውስጣችን እንዲያድል ለእርሱ በመፍቀድ ነው—ኤፌ. 3፡17፤ ዕብ. 11፡1።

ረ. በዚህ መንገድ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ጤነኛ እንሆናለን፣ መንፈሳዊነታችንም ምንም ለየት ያለ ነገር የሌለው የዘወትር እና የወትሮ ይሆናል—ሮሜ 8፡4፣ 6፤ ገላ. 5፡22-23።

**III. በመለኮታዊው እደላ ውስጥ የሆነው የዘወትር ሕይወት በመለኮታዊው ኢኮኖሚ ተዓምራዊ-መደበኛነት (miraculous normality) መሠረት ነው—1 ጢሞ. 1፡4፤ ኤፌ. 3፡9፦**

ሀ. የክርስቶስ፣ የመንፈስ፣ የሦስታንዱ አምላክ እና ከመለኮታዊው ባሕርይ ጋር የመለኮታዊው ሕይወት ልምምዶች ሙሉ በሙሉ መደበኛ (Normal) ናቸው—ቁ. 16-17።

ለ. ለልምምዳችን እና ለድሰታችን በእግዚአብሔር የሚሰጡን መንፈሳዊ እና መለኮታዊ ነገሮች ሁሉ መደበኛ ናቸው፤ ሆኖም ግን፣ እነዚህ መደበኛ ነገሮች ተዓምራዊ ናቸው፣ ስለዚህም ምክንያት ስለ መለኮታዊው ኢኮኖሚ ተዓምራዊ-መደበኛነት ልንናገር እንችላለን—1 ጢሞ. 1፡4፤ ኤፌ. 3፡9።

ሐ. ዳግም መወለድ ታላቁ ተዓምር ነው፣ ሆኖም ግን የሚከናወነው መደበኛ በሆነ መንገድ ነው፤ ስለዚህም ዳግም መወለድ ተዓምራዊ የሆነ መደበኛ ነገር፣ በክርስቲያን ሕይወታችን ተዓምራዊ-መደበኛ ነገር ነው—ዮሐ. 3፡3፣ 5-6፣ 8፤ 1 ጴጥ. 1፡23።

መ. የጌታን ስም መጥራት መደበኛ ነው፣ ሆኖም ግን ተዓምራዊ ከመሆኑ የተነሣ ስንጠራ በሂደት ያለፈውን እና የተጠናቀቀውን ሦስታንዱን አምላክ በጠቅላላ እንቀበላለን—ሮሜ 10፡12፤ ኤር. 33፡3።

*© 2022 Living Stream Ministry*